129
ለ1ኳ

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# CUSTOMS COMMISSION

ቀን ሐዳር 04 2012
Date
ቁጥር 4/0321/12
Ref.No.

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡- አስቀድሞ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ፤

ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ቀረጥና ታክስ በዛብን በማለት ቅሬታ የሚያቀርቡና አስቀድመው የከፈሉት ቀረጥና ታክስ እንዲመለስላቸው በመጠየቅ ዕቃው በባለሥልጣኑ እንዲወገድ የሚፈቅዱ አስመጪዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2(51) እና ከአንቀጽ 61 እስከ 64 ያሉ ድንጋጌዎች እንዲሁም አንቀጽ 76 እና 124 እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው የሚደረግ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በየጊዜው ለሚቀርቡ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እንዲቻል ከገቢዎች ሚኒስቴር አስተያየትና ማብራሪያ የተላከልን ሲሆን የተሰጠውን የህግ አስተያየት መሠረት በማድረግ የሥራ መመሪያ /ሰርኩላር/ ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ተሽከርካሪው አገር ውስጥ የገባበት አኳኋን ህግን የማይፃረር ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚመነጨው ወደ አገር ውስጥ በገባው ዕቃ ከመጠቀም መብት ነው፡፡ በመሆኑም የአዋጁ አንቀጽ 64(4) የገበያ ዋጋ ባላቸው የተተው ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ስለሆነም አስመጪው በፁሑፍ ያስወረሰው ተሽከርካሪ በሚሆንበት ጊዜ ተሽከርካሪው ተሸጦ ቀረጥና ታክሱን ከነወጪው ቢሸፍንም ባይሸፍንም አስመጪው በዕቃው ላይ የተወሰነውን ቀረጥና ታክስ መክፈል እንደማይችል ወይም በአዋጁ አንቀጽ 76 መሠረት የቀረጥና ታክሱን 5% ከፍሎ ዕቃው ወደ መጣበት እንዲመለስ ማድረግ የማይችል መሆኑን በመግለጽ አስቀድሞ የከፈለው ቀረጥና ታክስ እንዲመለስለት ከጠየቀ በአዋጁ አንቀጽ 61(1) መሠረት ዕቃውን እንደማይወስደው ገልጾ በጽሑፍ እንዲያረጋግጥ በማድረግና በአዋጁ አንቀጽ 124(2) መሠረት በዕቃው ላይ ሌላ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሊፈፀምበት እንደማይችል በማረጋገጥ በአዋጁ አንቀጽ 15(2) እና 124(1)(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት አስመጪው አስቀድሞ የከፈለው ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሊደረግለት ይገባል፡፡

02/03/2012

09/03 2012


አ.ከ.አበባ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ

AAK

የደብዳቤ ቁጥር

የደረሰበት ቀን 5/3/12

የተቀባዩ ስም

ፊርማ

የተመራለት የሥራ ሂደት/ቡድን

የገቢው ክርድ ቁጥር

የተመዘገበበት ቀን

መለያ ቁጥር 2

ስለሆነም ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ቀደም ሲል ቀረጥና ታክስ ተከፍሎት አገር ውስጥ የገባ ዕቃን አስመጪው ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መክፈል ባለመቻል ተሽከርካሪው በጉምሩክ እንዲወረስ በፁሑፍ አረጋግጦ ያመለከተ እንደሆነ ተሽከርካሪው በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ ቢወገድም ባይወገድም አስመጪው አስቀድሞ የከፈለውን የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ በአዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ በፁሑፍ ያቀረበ እንደሆነ በቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሥርዓት ወዲያውኑ እንዲመለስለት የተወሰነ ስለሆነ በዚሁ አግባብ ተፈፃሚ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.1

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለገቢዎች ሚኒስቴር ጽ/ቤት
  <u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

- ለቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለኤርፖርት ጉምሩክ /ቅ/ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ
- ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዳማ
- ለሐዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሐዋሳ
- ለባህር ዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ባህር ዳር
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  መቀሌ
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ድሬዳዋ
- ለጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅማ
- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅግጅጋ
- ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ኮምቦልቻ
- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞያሌ
- ለሚሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሚሌ
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጋላፊ
- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞጆ